# ታላቁ ሩጫ

(The Great Race)

በሱዛን ከሚንግስ
(by *Susan Cummings*)
ሜይ 6፥2004 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) [ባህሳ ማሌዢያ]

የተሰበሰው ሕዝብ ድምፅ እንደ ንብ ድምፅ ነበር አየሩንም ደስታ በስሜት ሞልቶታል። በዋናው መንገድ ላይ የተሰለፉ ብዙ ሰዎች ነበሩ፥ በአንድ ላይ ተከማችተው፥ የሩጫውን ማለቅ እየተጠባበቁ። አብዛኞቹ ለረዥም ሰዓት ጠብቀዋል፥ እናም መጨረሻው እንዲመጣ ተዘጋጅተዋል። ሌሎች ደግሞ ቀስ በቀስ ነው የመጡት፥ አሁን የሕዝቡ ክምችት ታላቅ ክምችት ሆኖ አድጓል።

ሩጫው ለተወሰነ ጊዜ እየተሮጠ ነበር፥ እና ብዙ የተቀላቀሉ ነበሩ። እንደአብዛኛዎቹ ሩጫዎች፥ ብዙዎች በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት አቋርጠዋል፥ እንዲሁም ብዙዎች ደግሞ ከጽናት ማጣት የተነሳ አቋርጠዋል። ይህን ዙር እየሮጡ ያሉት ከፊታቸው ለሚመጡትና በሩጫው ውስጥ ቀጣዩን ክፍል የራሳቸውን ድርሻ ለሚወጡት ችቦውን ለማቀበል ነው።

ጉባኤው የመጀመሪያውን ችቦ ያዥ የተለጠጠውን የመሮጫ ሜዳ ለመፈጸም ሲቃረብና በእይታቸው ሲገባ እጅግ በደስታ ስሜት ሲሞሉ ይሰማኛል። ሯጩ በጣም ደማቅ ባለ ቀይ ቀለም ትጥቅ አድርጓል እናም ችቦውን ከፍ አድርጎ በእጆቹ ይዟል። በጣም ደክሞት ነበር፥ እንዲሁም ሩጫውን ለመሮጥና ለመጨረስ በጣም በደስታ ስሜት ነበር። ወደ ስፍራው ሮጠ በእርግጥም፥  ሌላ ሯጭ ችቦው ወደ እርሱ እስኪመጣ እየጠበቀ ቆሟል። ለዚህኛው ሯጭ ታላቅ አድናቆት ተቀሰቀሰ እናም አሁን ችቦውን ይዞ መሮጥ የጀመረው አዲሱ አጋር ነው።

ከዚያም፥ ለ አንድ ወይም ሁለት ደቂቃ ጸጥታ ሆነ፥ እናም ሌላ ሯጭ ወደ እይታ ገባ። ይህኛው ሯጭ ደማቅ ቡኒ ትጥቅ አድርጓል፥ ይህም ደግሞ ችቦውን ከፍ አድርጎ ይዞ ነው የሚሮጠው። እርሱም ደግሞ ወደ መጨረሻው መድረሱን ስላየ በጣም ደስተኛ ነበር። ከጉባኤው ታላቅ አድናቆት ተሰጠው። ችቦውንም እንዲያቀብለው ተዘጋጅቶ ሲጠብቀው ለነበረው ሰው አቀበለ። ይሄኛውም ከዚያ ሩጫውን ጀመረ።

ከብዙ ደቂቃዎች በኋላ፥ ሁለት ተጨማሪ ሯጮች ወደ እይታ ገቡ። ሁለቱም ደማቅ ቀለም ያላቸው ትጥቆችን አድርገው ነበር። የአንዱ አረንጓዴ፥ የሌላኛው ደግሞ ብርቱካናማ ነበር። ሁለቱም  አንዱ አንዱን በሩጫው እንደሚያግዝ በጋራ ይሮጡ ነበር። ማናቸውም አይፎካከሩም፥ ነገር ግን አንዱ በአንዱ እይታ ውስጥ ይሮጡ ነበር። እነርሱም ደግሞ ለሚጠብቋቸው ችቧቸውን አቀበሉ። ጉባኤው አጨበጨበላቸው ነገር ግን አላደነቃቸውም።

ብዙዎች መምጣታቸውን ቀጠሉ፥ እናም ጉባኤው ስሜቱ ቀዝቀዝ ያለ ይመስላል። የመጀመሪያዎቹ ሯጮች ሞገድ በእይታቸው ሲያልፉ ከነበራቸው የመጀመሪያ ስሜት በኋላ፥ የተሰላቹ ይመስላሉ። ሯጮቹ ራሳቸው ደግሞ እንዲሁ ብዙም በጉጉት አልነበሩም፥ እንዲሁም በውድድሩ ውስጥ በከፍታ ስላልፈጸሙ በመጨረሳቸው እንኳን ደስተኞች አልነበሩም።

እየተመለከትሁ ሳለ፥ ከመጀመሪያዎቹ ጥቂት ሯጮች ካገኙት ቅጽበታዊ የደስታና የመነቃቃት ስሜት በኋላ፥ አንዳንዶቹ ሰዎች መሄድ ጀመሩ። አንዳንዶቹ ሌሎቹ ሯጮች ሩጫውን ለመሮጥ እየፈጀባቸው ባለው ጊዜ ርዝማኔ ማንጎራጎር ጀመሩ። አንዳንዶቹ እንዲያውም ችቦውን ለመቀበል ቦታቸው እንኳን ለመሆን እንዳልፈለጉ አየሁ፥ ምክንያቱም ውጤቱ ምንም ስለማይጠቅማቸው፥ እናም በመሮጣቸው እውቅናም ሆነ ሽልማትን ስለማያገኙ።

ድባቡ እየደበዘዘ መምጣት ጀምሮ ነበር፥ ኢየሱስ በርምጃ ወደላይ ሲመጣ አየሁ። በውድድሩ ውስጥ ነበር እናም በእሳት የሚቀጣጠሉ እጆቹን ወደ ውጭ ዘርግቶ በመሮጫው ማማ(ትራክ) ላይ ወደታች እየሄደ ነበር። ህያው ችቦ (ፋና) ነበር። የደመቀ ልብስ አልለበሰም ነበር፥ ነገር ግን ከጉልበቱ ትንሽ ዝቅ ብሎ በተንጠለጠለ ቀለል ያለ ልብስ ነበር። ሁሉም ዝም ብሎ ተመለከተው፥ ነገር ግን ማንም እሣቱን ከእጁ የሚወስድ አልነበረም። ማንም አድናቆት የሚሰጥ አልነበረም፥ ማንም አላጨበጨበም፥ ማንም በደስታ ስሜት ውስጥ አልነበረም። ማንም አልተነቃነቀም (ምንም አልመሰላቸውም)።

ኢየሱስ የሚቀጣጠሉ እጆቹን ዘርግቶ በሰዎቹ አጠገብ አለፈ። ማንም ግን ወደ ፊት አልመጣም።

ከዚያም፥ ረዥም ከሚመስል አፍታ በኋላ፥ ማንም ለምን ወደ ፊት እንዳልመጣ እያሰላሰልሁ ሳለ፥ አንድ ትንሽ ልጅ፥ እድሜው 5 ወይም 6 ዓመት ገደማ የሚሆን፥ ከሕዝቡ መሀከል ወጣ። በትናንሽ እጆቹ ወደ ኢየሱስ ዘረጋ፥ ከዚያም እሣቱን ሊይዝ እንደሚችል ጠየቀ። ኢየሱስ ፈገግ አለ፥ እናም ዝቅ አለ፥ ከዚያም ለልጁ ሰጠው። እሣቱ ወደ ልጁ እጆች ላይ ተሸጋገረ፥ እናም ልክ የኢየሱስ እጅ እንደነበረው እጆቹ እየተንቦገቦጉ በመሮጫ ትራክ ላይ ቁልቁል ሮጠ።

ከዚያም ኢየሱስ ወደ ሕዝቡ ተመለከተ።

ቀጥሎም ጌታ እንዲህ አለ፡ "*ሰዎች ዝና፥ ሀብትና የሰዎችን ጭብጨባ ይሻሉ። ለመሮጥና የሌላውን ሰው መጎናጸፊያ፥ ቅባትና ደረጃ ለመውሰድ ቀዳሚዎች ይሆናሉ። በደስታ ይጮኻሉ፥ ያጨበጭባሉ፥ እናም በመስመሩ ለመግባትና ከሌላ ሰው ራዕይ ጋር ለመሮጥ እርስ በእርሳቸው ይጎሻሸማሉ (ይገፋፋሉ)፥ ነገር ግን የራሳቸውን ከእኔ ለማግኘት ዋጋ አይከፍሉም።*"

"*መልካም በሆነ ጊዜና ሽልማት ባለ ጊዜ፥ እንዲሁም የሚያያቸው ሕዝብ ባለ ጊዜ፥ እንዲሁም በእነርሱ ላይ የሚደገፉ ሌሎች እንዳሉ ወይም እነርሱን በመንገድ የሚደግፋቸው እንዳለ ባወቁ ጊዜ ይሮጣሉ። ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ከፍ ማድረግ፥እንዲሁም ራሳቸውንና የደረሱበትን ደረጃ ማስተዋወቅን ይወዳሉ።*"

"*ሯጮቼ ወዴት ናቸው?*"

"*ስለጥሪያቸውና ስለወንጌል ብለው የሚሮጡት ወዴት ናቸው?*"

"*እኔን ብቻ ለማስደሰትና ሊጠቀሙባቸው ብቻ በሚፈልጉት ሰዎች ላለመታየት የሚሹት ወዴት ናቸው?*"

"*የሌሎች ሰዎችን መጎናጸፊያ፥ ቅባት፥ እንዲሁም ደረጃን ፍለጋ ያልሆኑት፥ ነገር ግን የራሳቸውን ፈንታ (ድርሻ) የሚሹት ወዴት ናቸው?*"

"*እኔ በፊታቸው ያስቀመጥሁላቸውን ሩጫ በጽናትና በሀሴት የሚሮጡት ወዴት ናቸው?*"

"*የት ነው ያሉት?*"

"*እላችኋለሁ፥ ከሀሰተኞቹ ጥላ አሁን ወደ ፊት እየወጡ ነው፥ እናም ስለሌሎች ሰዎች ችቦዎች አይጨነቁም፥ ነገር ግን ከእኔ የሚወጣውን እሣት ይፈልጋሉ፥ እኔም እለኩሳቸዋለሁ። በሰው የተሰጠን ችቦ አይይዙም፥ ነገር ግን ሁሉም እንዲያዩ ህያዋን ችቦዎች ይሆናሉ። ሰው እሣቱን ሊያስተላልፍም ሆነ ሊያስመስለው አይቻለውም። በአባቴ ብቻ የሚሰጥ ነውና። ቅዱስ ነው። ዋጋ የሚያስከፍል ነው። የእኔ እውነት ነው።*"

"*የእኔ ችቦ መሆን የሚያስከፍለውን ዋጋ ስለሚያውቁት፥እነዚህ ወደፊት ሲሮጡ ሰዎች እልል አይሉም። ስለእኔ የሚነዱትን ቁልቁል (በንቀት) ያዩአቸዋል፥ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ አሁን ለእኔ ለሚሮጡት ዓለም አይገባቸውም። ሽልማታቸውን በገነት ከአባቴ እንጂ ከሰው አይቀበሉም።*"

“*በእውነተኛ እሣት ፥ በቅድስናዬ እሣት ይሮጣሉ። ወደ ጨለማው ውስጥ ይሮጣሉ ቃሌንም ይለቅቃሉ።*”

“*ሀሰተኛው እሣት ድርሻውን ሮጧል ፥ እናም አሁን የእኔ የተደበቁት ወደ ፊት ይመጣሉ።*”

**ተፈጸመ።**

በሱዛን ከሚንግስ ፥ ሜይ 6 ፥ 2004 ዓ.ም (እ.ኤ.አ) ከሰዓት 11:17 ላይ

## አጋዥ ጥቅሶች

ሐዋርያት.20:24 ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።

ዕብራውያን.10:32-33 ነገር ግን ግማሽ በነቀፋና በጭንቅ እንደ መጫወቻ ስለ ሆናችሁ ግማሽም እንዲህ ካሉት ጋር ስለ ተካፈላችሁ ፥ ብርሃን ከበራላችሁ በኋላ መከራ በሆነበት በትልቅ ተጋድሎ የጸናችሁበትን የቀደመውን ዘመን አስቡ።

ወደ ኤፌሶን 2:10 እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።

1ጢሞቴዎስ.6:12 መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል ፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ።

2ጢሞቴዎስ.4:7-8 መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል ፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ዮሐንስ 1:9-10 ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ ዓለም ይመጣ ነበር። በዓለም ነበረ ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ ፥ ዓለሙም አላወቀውም።

2ቆሮ.4:6 በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ፥ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።

ኤፌ5:9-10 የብርሃኑ ፍሬ በበጎነትና በጽድቅ በእውነትም ሁሉ ነውና ለጌታ ደስ የሚያሰኘውን እየመረመራችሁ ፥ እንደ ብርሃን ልጆች ተመላለሱ፤

ፊል2:16 በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ ፥ ስለዚህም በከንቱ እንዳልሮጥሁ በከንቱም እንዳልደከምሁ በክርስቶስ ቀን የምመካበት ይሆንልኛል።

ዘካ.12:6፤ በዚያ ቀን የይሁዳን አለቆች በእንጨት መካከል እንዳለ ትንታግ ፥ በነዶችም መካከል እንዳለ እንደ ፋና ነበልባል አደርጋቸዋለሁ፤ በቀኝና በግራ በዙሪያ ያሉትን አሕዛብ ሁሉ ይበላሉ፤ ከዚያም ወዲያ ኢየሩሳሌም በስፍራዋ በኢየሩሳሌም ትኖራለች።

ሕዝ.1:13፤ በእንስሶቹ መካከል እንደሚነድድ የእሳት ፍም ያለ ምስያ ነበረ፤ በእንስሶች መካከል ወዲህና ወዲያ የሚሄድ እንደ ፋና ያለ ምስያ ነበረ፤ ለእሳቱም ፀዳል ነበረው ፥ ከእሳቱም መብረቅ ይወጣ ነበር።

በመንፈስ ቅዱስ አብሮን ለሠራ ለአምላካችን ለእስራኤል ቅዱስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምስጋና ይሁን ፥ አሜን።
ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ ትርጉም ሙሉነህ አዲሱ
Translated to Amharic by Muluneh Addisu, shalommuluneh@gmail.com